የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ
# FEDERAL NEGARIT GAZETA
OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሦስተኛ ዓመት ቁጥር ፳
አዲስ አበባ — የካቲት ፲፰ ቀን ፲፱፻፹፱

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

3rd Year No. 20
ADDIS ABABA – 25th Feb. 1997

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፷፪/፲፱፻፹፱ ዓ.ም.
ለአዲስ አበባ ቦሌ ዓለም አቀፍ አውሮፕላን ማረፊያ ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ ከአፍሪካ ልማት ፈንድ ብድር ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ ....... ገጽ ፫፻፶፫

CONTENTS

Proclamation No. 62/1997
African Develpment Fund Loan Agreement for Financing the Addis Ababa Bole International Airport Development Project Ratification Proclamation ............................................. Page 353

## አዋጅ ቁጥር ፷፪/፲፱፻፹፱

## በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በአፍሪካ ልማት ፈንድ መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ

ለአዲስ አበባ ቦሌ ዓለም አቀፍ አውሮፕላን ማረፊያ ፕሮጀክት ከፊል ማስፈጸሚያ የሚውል መጠኑ ፲፱ ሚሊዮን ፭፻ ሺህ ዩ.ኤ (አሥራ ዘጠኝ ሚሊዮን አምስት መቶ ሺህ ዩኒትስ ኦፍ አካውንት) የሆነ ገንዘብ የሚያስገኘው የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በአፍሪካ ልማት ፈንድ መካከል እ.ኤ.አ ዲሴምበር ፳ ቀን ፲፱፻፺፮ በአቢጃን የተፈረመ በመሆኑ፤

ይህንኑ የብድር ስምምነት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የካቲት ፲፰ ቀን ፲፱፻፹፱ ዓ.ም ባደረገው ስብሰባ ያጸደቀው ስለሆነ፤

በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ ፶፭ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

፩. አጭር ርዕስ
ይህ አዋጅ "ለአዲስ አበባ ቦሌ ዓለም አቀፍ አውሮፕላን ማረፊያ ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ ከአፍሪካ ልማት ፈንድ ብድር ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ ቁጥር ፷፪/፲፱፻፹፱." ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

## PROCLAMATION NO. 62/1997

## A PROCLAMATION TO RATIFY THE LOAN AGREEMENT BETWEEN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE AFRICAN DEVELOPMENT FUND

WHEREAS, a Loan Agreement, between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the African Development Fund stipulating that the African Development Fund provide to the Federal Democratic Republic of Ethiopia a loan amount of 19,500,000 UA (ninteen million five hundred thousand Units of Account) for partly financing the Addis Ababa Bole International Airport Development Project, was signed in Abidjan, on the 29th day of December, 1996,

*WHEREAS*, the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified said Loan Agreement at its session held on the 25th day of February, 1997,

*NOW, THEREFORE*, in accordance with Article 55 sub-Articles (1) and (12) of the Constitution, it is hereby proclaimed as follows:

1. *Short Title*
This Proclamation may be cited as the "African Development Fund Loan Agreement for Financing the Addis Ababa Bole International Airport Development Project Ratification Proclamation No. 62/1997."

፪. <u>ትርጓሜ</u>

በዚህ አዋጅ ውስጥ "የብድር ስምምነት" ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በአፍሪካ ልማት ፈንድ መካከል እ.ኤ.አ ዲሴምበር ፳ ቀን ፲፱፻፺፮ በአቢጃን የተፈረመው ቁጥር ኤፍ/ኢቲኤች/ኤአይአር—ዲኢቪ/ ፺፮/ ፴፯ የብድር ስምምነት ነው።

፫. <u>የገንዘብ ሚኒስትሩ ሥልጣን</u>

የገንዘብ ሚኒስትሩ በብድር ስምምነቱ የተገኘውን ፲፱ ሚሊዮን ፭፻ ሺህ ዩ.ኤ (አሥራ ዘጠኝ ሚሊዮን አምስት መቶ ሺህ ዩኒትስ ኦፍ አካውንት) በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል።

፬. <u>አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ ከየካቲት ፲፰ ቀን ፲፱፻፹፱ ዓ.ም ጀምሮ የጸና ይሆናል።

አዲስ አበባ የካቲት ፲፰ ቀን ፲፱፻፹፱ ዓ.ም.

ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ፕሬዚዳንት

2. *Definition*

In this Proclamation "Loan Agreement" means the Loan Agreement No. F/ETH/AIR-DEV/96/37 signed in Abidjan, on the 20th day of December, 1996 between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the African Development Fund.

3. *Power of the Minister of Finance*

The Minister of Finance is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the loan amount of 19,500,000 UA (nineteen million five hundred thousand Units of Account) in accordance with the terms and conditions set forth in the Loan Agreement.

4. *Effective Date*

This Proclamation shall enter into force as of the 25th day of February, 1997.

Done at Addis Ababa, this 25th day of February, 1997.

NEGASO GIDADA (DR.)

PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት
BERHANENA SELAM PRINTING ENTERPRISE